ECLA

Ethiopian Community Los Angeles

የኢትዮጵያውያን ማህበረሰብ ሎስ አንጀለስ

# የኢትዮጵያ ማህበረሰብ ሎስ አንጀለስ
# (ኢማሎአ)
# የመተዳደሪያ ሕገ ደንብ (2019)

# ETHIOPIAN COMMUNITY LOS ANGELES (E C L A) BYLAWS 2019

ማውጫ


| | |
|---|---|
| መቅድም | 1 |
| ሞዕራፍ አንድ ምስረታ | |
| አንቀጽ 1 ስያሜ | 1 |
| አንቀጽ 2የደንቡ ተፈጻሚነት | 1 |
| አንቀጽ 3 የማህበሩ የሥራ ቋንቋ | 1 |
| አንቀጽ 4 አድራሻ | 1 |
| አንቀጽ 5 ትርጓሜ | 1 |
| አንቀጽ 6 ሰም አርማና ማሕተም | 2 |
| ምዕራፍ ሁለት አላማ | |
| አንቀጽ 7 የማሕበሩ አላማ | 2 |
| ምዕራፍ ሶስት የማሕበሩ የገቢ ምንጭ | |
| አንቀጽ 8 የገንዘብ ምንጭ | 3 |
| አንቀጽ 9 የአባላት የገንዘብ አስተዋጽኦ | 3 |
| ምዕራፍ አራት አደረጃጀት | |
| አንቀጽ 10 ጠቅላላ ጉባዔ | 4 |
| አንቀጽ 11 አማካሪ ሸንጎ | 4 |
| አንቅጽ 12 ቦርድ | 4 |
| አንቀጽ 13 የቦርድ ሊቀመንበር | 5 |
| አንቀጽ 14 የቦርድ ምክትል ሊቀመንበር | 6 |
| አንቀጽ 15 የቦርድ ጸሐፊ | 6 |
| አንቀጽ 16 የህዝብ ግንኙንት ሃላፊ | 6 |
| አንቀጽ 17 ገንዘብ ያዥ | 7 |
| አንቀጽ 18 ኦዲተር | 7 |
| አንቀጽ 19 የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ | 8 |
| አንቀጽ 20 ዳይሬክተር | 9 |
| አንቀጽ 21 ዋና ጸሐፊ | 9 |
| አንቀጽ 22 ልዩ ልዩ ኮሚቴዎች ስለ ማቋቋም | 10 |
| አንቀጽ 23 የዕቅድና ፕሮጀችት ጥናት ኮሚቴ | 10 |
| አንቀጽ 24 የሕግና ማህበራዊ ጉዳይ | 11 |
| አንቀጽ 25 የጤናና የስፖርት ኮሚቴ | 11 |
| አንቀጽ 26 የትምህርትና ስልጠና ኮሚቴ | 12 |
| አንቀጽ 27 የሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ኮሚቴ | 12 |
| አንቀጽ 28 የወጣቶች ጉዳይ ኮሚቴ | 12 |
| አንቀጽ 29 የአዛውንቶች ጉዳይ ኮሚቴ | 13 |

| | |
|---|---|
| ምዕራፍ አምስት የአባልነት መመዘኛ | |
| አንቀጽ 30 የአባልነት መመዘኛ | 13 |
| አንቀጽ 31 የአባላት መብት | 13 |
| አንቀጽ 32 የአባልት ግዴታዎች | 13 |
| አንቀጽ 33 ከአባልነት የሚያስወግዱ | 14 |
| አንቀጽ 34፡-ከቦርድ አባልነት የሚያስወግዱ ድርጊቶች | 14 |
| አንቅጽ 35፡- ከቦርድ አባልነት ለመልቀቅ የሚሻ/የምትሻ | 14 |
| አንቀጽ 36 ተጠያቂነትን በተመለከተ | 15 |
| አንቀጽ 37 የጥቅም ግጭት | 15 |
| አንቀጽ 38 ሚስጥር ስለመጠበቅ | 15 |
| ምዕራፍ ስድስት ልዩልዩ ድንጋጌዎች | |
| አንቀጽ 39 የምርጫና የድምጽ አሰጣጥ ሥነ ስርዓት | 15 |
| አንቀጽ 40 አስመራጭ ኮሚቴ | 16 |
| አንቀጽ 41 የቦርድ አባላት አመራረጥ | 16 |
| አንቀጽ 42 የአገልግሎት ዘመን | 16 |
| አንቀጽ 43 የመተዳደሪያ ደንቡ የሚሻሻልበት ሁኔታ | 16 |
| አንቀጽ 44 ማሕበሩ የሚፈርስበት ሁኔታ | 16 |
| አንቀጽ 45 የበጀት ዓመት (ዘመን) | 17 |
| አንቀጽ 46 መተዳደሪያ ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ | 17 |
| አንቀጽ 47 ትርጓሜ | 17 |

## መቅድም

እኛ በሎስ አንጀለስና አካባቢው የምንኖር ኢትዮጵያዊያንና ኢትዮ-አሜሪካዊያን በራሳችን ፈቃድ በአዲስ መልክ በመደራጀት የማህበረሰባችንን ችግሮች በጋራ ለመቋቋም፣ድንቅ የሆኑ የጋራ ባህላዊ ዕሴቶቻችንን ለመጠበቅ፣ከምንኖርበት አገር ባህል ህግና የኑሮ ዘይቤ በማጣጣም ውጤታማ እንድንሆን በሁለንተናዊ መልኩ የሚያግዝ ከማንኛውም የዘር ፣የፖለቲካና የሐይማኖት አመለካከት ልዩነቶች ነፃ የሆነ ጠንካራ ማህበር እንዲኖረን በመፈለግና እንዲሁም የእርስ በእርስ የመቀራረብ፣ የመግባበት፣ የመረዳዳትና የመተጋገዝ ባህላችንን በማዳበርና በአሁኑ ጊዜም ለኢትዮጵያውያን ወገኖቻቸው በግልም ሆነ በድርጅት መልክ የተለያዩ አገልግሎቶችን በመስጠት ላይ ያሉትን በአንድ ላይ አስተባብሮና አዋህዶ በመያዝ ሰፋ ያለ የተሻለ ውጤታማ የሆነ አገልግሎቶችን ለመስጠት እንድንችል በማሰብ ሁሉን አቀፍ የሆነ የኢትዮጵያውያን ማህበረሰብ በሎስ አንጀለስን ለማቋቋም ይህን የመተዳደሪያ ደንብ (Bylaw) በዛሬው ቀን SEPTEMBER 28,2019 አፅድቀናል።

## ምዕራፍ አንድ፡- ምሥረታ (ESTABLISHMENT)

አንቀጽ 1፡- ስያሜ

የማህበሩ መጠሪያ ስም “የኢትዮጵያ ማህበረሰብ ሎሰ አንጀለስ” (ETHIOPIAN COMMUNITY LOS ANGELES.( E . C. L. A) ተብሎ ይጠራል

አንቀጽ 2፡- የደንቡ ተፈጻሚነት ወሰን

ይህ ደንብ በሎስ አንጀለስ ከተማ እና በሌሎች በአካባቢው በሚገኙ ከተሞች ውስጥ በሚኖሩ የማህበሩ አባላት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል

አንቀጽ 3፡- የማህበሩ የሥራ ቋንቋ አማርኛና እንግሊዘኛ ይሆናል

አንቀጽ 4፡- አድራሻ

የማህበሩ ዋና ጽሕፈት ቤት በሎስ አንጀለስ ከተማ ይሆናል

አንቀጽ 5፡- ትርጓሜ

በዚህ መተዳደሪያ ደንብ ውስጥ፡-

5.1 ኢትዮ አሜሪካዊ ፡- ማለት በትውልድ ኢትዮጵያዊ ወይም አሜሪካዊ ከኢትዮጵያን ቤተሰብ የተወለደ/ች ወይም ከኢትዮጵያዊያን ቤተሰብ ጋር የጋብቻ ትስስር ያለው/ላት የአካባቢው ህጋዊ ነዋሪ የሆነ/ች የማህበሩ አባል ነው።

5.2 ሎስ አንጀለስ እና አካባቢው፡- ማለት በሎስ አንጀለስና አካባቢው በሎሰንጀለስ ፣ኦሬንጅ፣ሳንበርናንዲኖ፣ ሪቨርሳይድና ቬንቹራ ካውንቲ ውስጥ በሚገኙ ከተሞች የሚኖሩ የማህበሩ አባላት ነው።

5. 3 አባል፡- ማለት የአባልነት መመዘኛውን በማሟላት ግዴታውንም በአግባቡ የሚወጣ ሰው ሲሆን ይህም በሁሉም የማህበሩ የሥራ ሀላፊነት ተመርጦ የሚያገለግሉትንም ያጠቃልላል፡

5.4 ቤተሰብ ፡- ማለት የአባሉ ወይም የአባሏ የትዳር ጓደኛና ልጆች አብረዋቸው የሚኖሩ አባት ወይም እናት፡

5.5 ማህበር፡- ማለት የኢትዮጵያ ማህበረ ሰብ ማህበር በሎስ ኣንጀለስ ማለት ነው ፡

5.6 ኢ . ማ . ሎ አ፡- የኢትዮጵያ ማህበረሰብ በሎስ አንጀለስ ማለት ነው፡

5.7 ጠቅላላ ጉባኤ ፡- ማለት የአባልነት መመዘኛውንና ግዴታውን የተወጣ መላውን አባላት የሚያካትት፡ ሲሆን የማህበሩ ወሳኝ የበላይ አካል ነው።

5.8 ቦርድ፡- ማለት በጠቅላላው ጉባኤው አጠቃላይ ስብሰባ የሚመረጥ 11 አባላትን ያካተተ ማህበረሰቡን በበላይነት የሚያስተዳድር አካል ነው።

5.9 የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ፡- ማለት በቦርዱ የሚመረጡ ወይም የሚመደቡ የማህበሩን የዕለት ከዕለት የሥራ እንቅስቃሴ የሚያከናውኑ ናቸው።

5.10 ዳይሬክተር፡- ማለት በቦርድ የሚመረጥ ወይም የሚቀጠር የሥራ አስፈጻሚውን ኮሚቴ በሀላፊነት የሚመራና ማህበሩን የሚወክል ነው።

አንቀጽ 6፡- ስም ዓርማና ማህተም

በአንቀጽ 1 በተጠቀሰው የስም ስያሜና በዚህ መተዳደሪያ ደንብ ሽፋን ላይ የሚገኘውን አርማ በማስመሰል፣ በመለወጥ ቃላት በመጨመር ወይም በመቀነስ መጠቀም በሕግ የተከለከል ነው።

## ምዕራፍ ሁለት፡-ዓላማ (OBJECTIVES)

አንቀጽ 7፡- የማህበሩ ዓላማዎች

የኢትዮጵያ ማህበረሰብ በሎስ አንጀለስ (E. C. L A) የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

7.1. በሎስ አንጀለስና አካባቢው የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮ-አሜሪካውያን በመቀራረብ የጋራ ባህሎቻቸውንና ታሪካቸውን እንዲያዳብሩ ምቹ የጋራ መድረኮችን መፍጠር

7.2. የሐይማኖት የፆታ የፖለቲካ የብሔርና የዕድሜ ወዘተ ልዩነት ሳይኖር ማንኛውም የማህበሩን ደንብ የተቀበለ/ች ኢትዮጵያዊ ወይም ኢትዮ-አሜሪካዊ የሆነ ሁሉ አንድ ጠንካራ የሆነ ማህበረሰብ (Community) በማቋቋም የጋራ መብትን ለማስከበር ይቻል ዘንድ ድርጅታዊ ሃይል ለመፍጠር፣

7.3. በሞት፣ በሕመም፣በአደጋ፣በሥራ እጦትና በአካል መጓደል ችግር ለሚገጥማቸውና እንዲሁም አዲስ ለሚመጡ ኢትዮጵያውያን ያለ ብዙ ችግር በቀላሉ ወደ አሜሪካን የአኗኗር ዘይቤ እንዲሸጋገሩ የሚያስችለውን ዘዴ ማመቻቸትና ማገዝ

7.4. የማህብረሰቡ አባላትና ቤተሰብ ለጤናማ አኗኗር የጋራ አገልግሎት መጠቀሚያ የሚሆን የትምህርት ስልጠና፣ የጤና አጠባበቅ፣ የአካል ማደበሪያና የመዝናኛ ወዘተ በአጠቃላይ ሁሉን አቀፍ የሆነ የማህበረሰብ (COMMUNITY) ማዕከል መፍጠር
7.5. የማህበረሰባችን ወጣቶች ከአጉል ባህል ከወንጀል ከአልባሌ ሱስ ነፃ እንዲሆኑ የምክር የስልጠናና መልሶ የማቋቋሚያ ድጋፍና ዕርዳታ መስጠት
7.6. በህብረተሰባችን ውስጥ ለሚገኙ አዛውንት ( እናትና አባት ) የሚውሉበትና የሚዝናኑበት አገልግሎት ማመቻቸት
7.7. በሎስአንጀለስና አካባቢው የሚኖሩ በማህበረሰባችን አባሎች ላይ የሰብአዊ መብትና የፍትህ መጓደል ቢከሰት በጋራ ችግሩን ለመቋቋምና ለመከላከል፣ ወጣቶች የነፃ ትምህርት ዕድልና የማህበራዊ አገልግሎቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ እገዛና ድጋፍ ለመስጠት።
7.8. በማህበረሰብቻን ውስጥ የሚገኙትን የህክምና ባለሙያና እንዲሁም የማህበራችን የሆኑትሐኪሞች
ጭምር ዕውቀታቸውን የሚጠይቅ ቅድመ ዝግጅት አዘል የሆነ ትምህርትና ዕርድታ ማዘጋጀት የማህበረሰባችንን ወጣት ልጆች በአዕምሮ መታወክ በኦቲዝም፣ በካንሰር እንዲሁም የመሳሰሉትን ህመሞች እንዴት መከላከልና ማዳንም ጭምር የያዘ ትምህርት ማዘጋጀት
7.9. ከትውልድ ሀገራችን ኢትዮጵያ ጋር ማህበረሰባችን የሚኖረውን ሃገራዊና ባህላዊ ትስስር ለማዳበር፣ለማጠናከርና አቅም በፈቀደ መጠን አገርንና ወገንን ለመርዳት የሚቻልበትን ሁኔታ ለማመቻቸትና ተግባራዊም ለማድረግ፡

## <u>ምዕራፍ ሶስት፡- የማህበሩ የገቢ ምንጭ</u>

አንቀጽ 8፡- የገቢ ምንጭ
ማህበሩ አላማውን ለማሳካት የሚጠቀምባቸው የገቢ ምንጭ፣

8.1. ከማህበሩ አባላት የሚሰበሰብ የመመዝገቢያና አመታዊ የአባልነት ክፍያ፡
8.2. የተለያዩ የገንዘብ ማሰባሰቢያ ዝግጅቶችን ተግባራዊ በማድረግ ከሚገኝ ገቢ፡
8.3. የፕሮጀክት ሀሳቦችን በማመንጨት መንግስታዊና ለጋሽ ለሆኑ ድርጅቶች በማቅረብ ከሚገኝ የገንዘብ ድጎማ፡
8.4. ከበጎ አድራጊ ግለሰቦችና ከማህበሩ አባላት የሚገኝ የገንዘብ ድጋፍ ነው፡

አንቀጽ 9፡- የአባላት የገንዘብ አስተዋጽዖ መጠን

9.1. የእያንዳንዱ የተመዘገበ የማህበሩ አባል ዓመታዊ ክፍያ በግለሰብ $60.00 ሲሆን፡ ክፍያው አቅምና ፍላጎት ያለው በአንድ ጊዜ መክፈል ይችላል (Amended Nov 28, 2020)
9.2. ባንድ ጊዜ መክፈል ካልቻለ በሩብ ዓመት (በ የ3 ወሩ) በግለሰብ $10.00 በቤተሰብ $15.00 በመክፈል የአመቱን ክፍያውን ያጠናቅቃል፡ የክፍያ፡ ወራቶች

የመጀመሪያው ሩብ ዓመት ክፍያ OCTOBER 10
የሁለተኛው ሩብ ዓመት ክፍያ JANUARY 10
የሶስተኛው ሩብ ዓመት ክፍያ APRIL 10
የአራተኛው ሩብ ዓመት ክፍያ JULY 10 ድረስ ይሆናል።

9.3. የአሜሪካ ህግ በሚደነግገው መሰረት በጡረታ የተገለሉ የማህበሩ አባላት የመመዝገቢያና
ዓመታዊ ክፍ አምሳ በመቶ ቅናሽ (50% discount) አላቸው

## ምዕራፍ አራት ፦ አደረጃጀት ሥልጣንና ተግባር (Organizational Structure, Powers and Duties)

### አንቀጽ 10፦ ጠቅላላ ጉባኤ

ጠቅላላ ጉባኤ የኢትዮጵያ ማህበረ ሰብ በሎስ አንጀለስ ዓላማ ለማራመድ የአባልነት ግዴታቸውን የሚወጡ አባላትን በሙሉ ያካተተ ስብስብ ሲሆን የሚከተሉት ተግባርና ሃላፊነት ይኖሩታል።

10.1. ወሳኝ የሆኑና በደንቡ ላይ የተመለከቱትን የማህበሩ ጉዳዮች የመጨረሻው ወሳኝ አካል ነው

10.2. ሶስት (3)የኦዲትና የቁጥጥር ኮሚቴ አባላትና አስራ አንድ(11) የቦርድ አባላትን ይመርጣል

10.3. ጠቅላላ ጉባኤው አንድ አመት ሲቀረው አምስት (5) የአስመራጭ ኮሚቴ አባላትን ይመርጣል

10.4. አምስት (5) የአማከሪ ሸንጎ አባላትን በጠቅላላ ጉባኤ ይመርጣል

10.5. በዓመት አንድ ጊዜ በመሰብሰብ ከሥራ አሰፈጻሚ ኮሚቴው፣ ከቦርዱ፣ ከኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ የሚቀርብለትን የሥራ አፈጻጸምና የፋይናንስ ሪፖርቶች አዳምጦ ውሳኔና መመሪያ ይሰጣል፤

10.6. የቦርዱ ሊቀ መንበር አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ከጠራ ይሰበሰባል፤

10.7. የተጓደሉ የሥራ መስኮች ካሉ በቦታው በምርጫ ይተካል

10.8. ዓመታዊ ባጀት ያፀድቃል አፈጻጸሙም ሕግና ደንብ የተከተለ መሆኑን ያረጋግጣል፣ መተዳደሪያ ደንቡን ያጸድቃል፣ አስፈላጊ ሲሆን ያሻሽላል

10.9. ከማሕበሩ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ (50%) በስብሰባ ከተገኙ ምልአተ ጉባኤ ይሆናል፣ምልአተ ጉባኤ ካልተሟላ ግን፣ በእለቱ ከተገኙት ውስጥ ¾ ( 75%) የእለቱ አጀንዳ እንዲቀጥል ከወሰኑ ስብሰባው ይካሄዳል ይሁን እንጂ በዕለቱ በስበሰባው ላይ የተገኙት አባላት ከጠቅላላ አባላት ቁጥር ቢያንስ ከ10% (ከአስር ከመቶ) በላይ መሆን ይኖርበታል።

### አንቀጽ 11፦አማካሪ ሸንጎ

የኢትዮጵያ ማሕበረሰብ በሎሰ አንጀለስ (ኢማሎአ) የአማካሪ ሸንጎ ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ተግባርና ሀላፊነት ይኖሩታል ተጠሪነቱም ለጠቅላላ ጉባኤው ይሆናል፡

11.1. የማሕበሩን እድገትና መዳበር አስመልክቶ ቦርዱ የአማካሪውን ሸንጎ ማሻሻያ ሃሳብ ለመጠየቅ ይችላል
11.2. አማካሪ ሸንጎው ስለማሕበራዊ ኑሮ፣ ሰለ በህል፣ ስለትምሕርትና ሕግ- ነክ ጉዳዮች ሁሉ ቦርዱን ያማክራል
11.3. በቦርድ አባላት፣ በቋሚ ኮሚቴ አባላት፣ወይም በጠቅላላ ጉባኤው መካከል አለመግባባት ቢፈጠርና ሁከት ቢነሳ፣ የማህበሩ አሠራር ቢተጓጎል፣ አማካሪ ሸንጎው በአስታራቂነት ሀላፊነቱን ወስዶ አወዛጋቢ ችግሮችን በማስወገድ አባላቱን ያስማማል።
11.4. በቦርዱ አካላትም ሆነ በድርጅቱ ውስጥ አለመግባባት ቢኖር፣ ውሳኔ ላይ ለመድረስ በማያስችልበት ጊዜ ወደ ሕጋዊ መንገድ ከመሔዱ በፊት፣ ሸንጎው ጉዳዩን ተመልክቶ በመካከላቸው የተፈጠረውን ችግር በውይይት እንዲፈታ ጥረት ያደርጋል፡ ስምምነት ላይ ለመድረስ የማይቻልበት ሁኔታ ከተፈጠረ ጉዳዩ ወደ ጠቅላላ ጉባኤው ይተላለፋል።

እንቀጽ 12፦ ቦርድ

የኢትዮጵያን ማህበረሰብ በሎስ አንጀለስ ቦርድ በጠቅላላ ጉባዔ የሚመረጡ አስራ አንድ (11) አባላት ይኖሩታል። የቦርድ ኣባላት የዕድሜን: የፃታን: የሃይማኖትን ተመጣጣኝ ስብጥር ያገናዘበ እንዲሆን (Amended Nov 28, 2020)

የማህበሩን ጠቅላላ የሥራ ክንውን የመተዳደሪያ ደንቡን ተከትሎ መከናወኑን የሚያረጋግጥ የበላይ አካል ሲሆን ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባኤው ይሆናል፣ ዝርዝር ተግባርና ሃላፊነቱም፡

12.1. ቦርዱ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሚያደርገው የሥራ እንቅስቃሴ የማህበሩን የመተዳደሪያ ደንብ የተከተለ መሆኑን ያረጋግጣል
12.2.የማህበሩ ንብረቶችና ገንዘብ በአግባቡ መያዙንና በሥራ ላይ መዋሉን ያረጋግጣል፡
12.3. የሥራ አስፈጻሚ አባላትን ይመርጣል ወይም ይመድባል፡
12.4. የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው የሚያደርጋቸው የውጭ ግንኙነቶች ከማህበሩ ዓላማ ጋር የማይፃረሩ መሆናቸውን ይቆጣጠራል፡
12.5. በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው የሚቀርብለትን የአጭርና የረጅም ጊዜ ዕቅድ ፣ ባጀት ፣ የፕሮጀክት ሃሳቦችን ( Project proposals) መርምሮ ያጸድቃል፡
12.6. በየሶስት ወሩ በመስብሰብ፡ የማህበሩን የሥራ እንቅስቃሴ ሪፖርት ከሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ያዳምጣል እርማትና የማስተካከያ መመሪያ ይሰጣል የቦርዱ አባላት ማህበሩ የሚጠናከርበትን አባላት ንቁ ተሳታፊ የሚሆኑበትን ዘዴ በማጥናትና በመከታተል ማሻሻያ ያደርጋል።
12.7. የቦርዱ ውሳኔ አሰጣጥ በአብላጫ ድምጽ ወይም ከ50% በላይ ያገኘው ወገን አሸናፊ ይሆናል።
12.8. የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የቋሚና የጊዜያዊ ሠራተኞች ቅጥርና የክፍያ መጠን ሲያቀርብ ያፀድቃል፡ ይህ ተግባራዊ  የሚሆነው ማህበሩ በቂ የገንዘብ አቅም ሲኖረው ነው፡

12.9. ከኢትዮጵያ ማህበረሰብ በሎስ አንጀለስ መተዳደሪያ ደንብ በማይፃረር መንገድ ቦርዱ የራሱን የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ ያዘጋጃል፡

12.10. ከ $3000.00 ( ከሶስት ሺ) በላይ የሚጠይቁ ወጭዎችን ያጸድቃል፡

12.11. እንደ አስፈላጊነቱ የተለያዩ ኮሚቴዎችን ያቋቀማል አስፈላጊ ሆኖ ካላገኘው እንዲፈርሱ ያደርጋል፡

12.12. ከአምስቱ ማለትም ሊቀመንበሩ ም/ሊቀ መንበሩ ጸሐፊው ገንዘብ ያዥውና የሕዝብ ግንኙነት ሀላፊው በስተቀር ሰድስቱ የቦርድ አባላት ከቦርድ አባል ተግባርና ሀላፊነት በተጨማሪ በተለያዩ ቦርዱ በሚያቋቁማቸው ኮሚቴዎች እንደአስፈላጊነቱ በሀላፊነት የሥራ ድርሻ ይኖራቸዋል

12.13. የሥራ ዘመኑ ሲያልቅ ወጭ ቦርድ ከአዲሱ ከገቢው ቦርድ ጋር ለመጀመሪያው ስድስት ወራት አብሮ በመሳተፍ የሽግግር ወቅቱ ቀጣይነት እንዲኖረው ትብብር ያደርጋል።

አንቀጽ 13፡- የቦርድ ሊቀመንበር

የቦርድ ሊቀ መንበር በጠቅላላ ጉባኤው የሚመረጥ ሲሆን ተጠሪነቱም ለቦርዱና ለጠቅላላ ጉባኤው ይሆናል፣ ዝርዝር ተግባሩና ሃላፊነቱም፣

13.1. የቦርዱን ስብሰባ በሊቀ መንበርነት ይመራል

13.2. የጠቅላላ ጉባኤን መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባ ይጠራል ስብሰባውን በሊቀ መንበርነት ይመራል

13.3. የቦርዱ አባላትና የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባለት በህገ ደንቡ መሰረት ተግባራቸውን ማከናውናቸውን ያረጋግጣል

13.4. የቦርድ አባላትና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ እንዲሁም ዳይሬክተሩ ሃላፊነታቸውን በብቃትና በትጋት እንዲወጡ ያበረታታል

13.5. የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴና ዳይሬክተሩ የመተዳደሪያ ደንቡን በመከተል በተለያዩ ኮሚቴዋች ምደባ ያዘጋጃል፡

13.6. በቦረዱ አባላት ሲፀድቅ በተግባር ያውላል፣

13.7. በገንዘብ ወጭ ማዘዟና በቼኮች ላይ መፈረም

አንቀጽ 14፡- የቦርድ ምክትል ሊቀ መንበር

ምክትል ሊቀመንበሩ በጠቅላላ ጉባኤው ይመረጣል ተጠሪነቱ ለቦርዱና ለጠቅላላ ጉባኤው ይሆናል ተግባርና ሃላፊነቱም፡

14.1. የምክትል ሊቀ መንበሩ የሥራ ድርሻ ከሊቀ መንበሩ ጋር ተመሳሳይ ሲሆን፣ ሊቀ መንበሩ በማይኖርበት ጊዜ ምክትል ሊቀመንበሩ በምትኩ ሥራውን ያከናውናል

14.2. በሊቀመንበሩ የሚሰጡትን የማስተባብርና የመቆጣጠር ተግባራት ያከናውናል

አንቀጽ 15 ፡- የቦርድ ፀሐፊ

በጠቅላላ ጉባኤው የሚመረጥ ሲሆን፣ተጠሪነቱም ለቦርዱና ለጠቅላላ ጉባኤው ይሆናል፣ የሚከተሉት ተግባርና ሀላፊነት ይኖሩታል።

15.1 ከሊቀመንበሩ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት የቦርድ ስብሰባና አስቸኳይ የጠቅላላ ጉባኤ ጥሪ ያስተላልፋል፡

15.2. የቦርዱንና የጠቅላላ ጉባዔውን የስብሰባ ቃለ ጉባኤ ይይዛል

15.3. በማንኛውም የቦርድ ስብሰባ ወቅት ያለፈውን ቃለ ጉባኤ በማንበብ እንዲፀድቅ ያስደርጋል፡

15.4. የቦርዱን የጽ/ ቤት ተግባራት ያከናውናል መዛግብትና መረጃዎችን ይይዛል

15.5. የማሕበሩን አባላት ዝርዝር መዛግብት ይይዛል

15.6. ወጭና ገቢ ደብዳቤዎችን ያዘጋጃል በሊቀ መንበሩ ሲፈረም ወደሚመለከተው ያስተላልፋል

15.7. በቼኮች ላይ መፈረም (Amended Nov 28, 2020)

15.8. በሊቀመንበሩ የሚሰጡትን ማንኛውንም ተጨማሪ ተግባራት ያከናውናል፣

አንቀጽ 16፡- የህዝብ ግንኙነት ሃላፊ

የህዝብ ግንኙነት ሃላፊ በጠቅላላ ጉባኤው የሚመረጥ ሲሆን የማህበሩን የሥራ እንቅስቃሴ በህዝብ መገናኛ ብዙሃን ፣ በበራሪ ወረቀቶች፣ በሬዲዮንና በኢንተርኔት ሚዲያዋች የሚሰራጩ መረጃዎችን የሚያቀናብር ሲሆን ተጠሪነቱም ለቦርዱና ለጠቅላላ ጉባኤው ይሆናል።

16.1. የማህበሩ አላማና የሥራ እንቅስቃሴ ለመገናኛ ብዙሃን የሚሰራጩ የማህበሩን ድረገጽ (Web-Site) ያስተዳድራል ወቅታዊ መረጃዎችን ያስቀምጣል፡

16.2. የጠቅላላ ጉባኤውን የቦርዱንና የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴውን ስብሰባ በቨዲዮ በመቅረጽ
ለመረጃ ያስቀምጣል።

16.3. የኮሚቴዎችን አቢይ የሥራ እንቅስቃሴ በቨዲዮ በመቅረጽ ለህዝብ የሚተላለፍበትን መንገድ ያዘጋጃል፡

16.4. የማህበሩን እንቅስቃሴ ለአባላት ለማሰራጨት በየ 6 ወሩ መጽሄት ያዘጋጃል፡

16. 5. ለሥራው እንቅስቃሴ የሚያስፈለጉትን ቁሳቁሶች ዝርዝርና ባጀት ያቀርባል ሲፈቀድ በሥራ ላይ ያውላል፡

16.6. በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚመለከታቸውን ሃላፊዎች ቃለ መጠየቅ በማድረግ ለአባላት የሚሰራጭ፡ መረጃዎችን
አቀነባብሮ ያዘጋጃል፡

16.7. በኮሚቴው ውስጥ በፈቃደኝነት አገልግሎት ለመስጠት የሚችሉትን በመመልመል በኮሚቴው ሲፈቀድ በሥራ ላይ ያውላል፡

16.8. ማንኛውም የጽሁፍ የኤሌክትሮሪኒክስ፡ የቃለ መጠይቅ፡ መግለጫዎች ሁሉ በሚዲያ ከመተላለፋቸው በፊት በዳይሬክተሩ ወይም በቦርድ መፈቀድ አለበት፡

16.9. አባላትን በማስተባበር ረገድ አስፈላጊ የሆኑትን ተግባራት በተገቢ መልኩ ይከታተላል ያስፈጽማል፡

16.10. ከመንግሥትና ከግል ድርጅቶች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ላይ ክትትል ያደርጋል አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝና በቦርዱ ሲጸድቅ መረጃ ይሰጣል፡
16.11. ማንኛውም የቦርድ አባል ማሕበሩን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ በመገናኛ ብዙሃን ወይም በሚዲያ ከማሰተላለፋቸው በፊት በቦርዱ መፈቀድ ይኖርበታል።

አንቀጽ 17 ፡-ገንዘብ ያዥ

የማህበሩ ገንዘብ ያዥ በጠቅላላ ጉባኤው የሚመረጥ ሲሆን ተጠሪነቱ ለቦርዱና ለጠቅላላ ጉባኤው ይሆናል ዝርዝር ተግባርና ሀላፊነቱም የሚከተሉት ናቸው።

17.1. የማሕበሩን ገንዘብ ገቢና ወጪ በሚዛናዊ የገንዘብ አያያዝ ዘዴ በመጠቀም ይቆጣጠራል
17.2. የማሕበሩ አባላት የመመዝገቢያና አመታዊ ክፍያ እንዲፈጽሙ ክትትል ያደርጋል
17.3. ማንኛውንም የገንዘብ ወጭ ከመፈረሙ በፊት የወጭ ማዘዣ ሰነድ በዳይሬክተሩ፣ በቦርዱ ሊቀመንበር ወይም ም/ሊቀመንበር መጽደቁን ማረጋገጥ
17.4. ማንናውም የገንዘብ ወጭ የማህበሩ ቼክ ሥልጣኑ በተሰጣቼው በሊቀ መንበሩ፣በዳይሬክተሩ ወይም በም/ ሊቀመንበሩ በሰስቱም ካልሆነም በሁለቱ በጣምራ መፈረም ይኖርበታል።
17.5. ማንኛውም ወደ ማህበሩ የሚላክ ወይም የሚገባ ገንዘብ በማሕበሩ ትክክለኛ ደረሰኝ ተመዝግቦ ለላኪው ወይም ለከፋዩ እንዲደርስ ያደርጋል፣ ደረሰኙም የማሕበሩ አርማ ያለበትና የቁጥር ቅደም ተከተል የያዘ መሆኑን ያረጋግጣል፡
17.6. ከማንኛውም የገቢ ምንጭ የተሰበሰበ ገንዘብ በ24 ሰአት ውስጥ ወደ ማሕበሩ ባንክ ገቢ መሆኑን ያረጋግጣል፡

አንቀጽ 18፡- የኦዲት ቁጥጥር ኮሚቴ

የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ አባላት በጠቅላላ ጉባዔው የሚመረጡ 3 የሂሳብ የንብረትና አስተዳደር ሙያተኞችን ያቀፈ ሲሆን ዝርዝር ተግባርና ሃላፊነቱም፣

18.1. የማሕበሩን የገንዘብ የሂሳብና የንብረት አያያዝ ደንብ በማዘጋጀት በቦርዱ ሲፀድቅ ለሚመለከታቸው
18.2. የሥራ ክፍሎች ያስተላልፋል የሥራ አስፈፃሚው የገንዘብና የሂሳብ ኮሚቴ ገንዘብና ሂሳብ በደንቡ መሠረት መከናወናቸውን በየ 6 ወሩና በማንኛውም ጊዜ እንደአስፈላጊነቱ የቁጥጥር ሪፖርት ያቀርባል፣
18.3. በአመት አንድ ጊዜ ዝርዝር የኦዲት ሪፖርት ለቦርዱ፣ ለሥራ አስፈፃሚና ለጠቅላላ ጉባኤው ያቀርባል፣
18.4. እንደአስፈላጊነቱ በማንኛውም ጊዜ የገንዘብም ሆነ የሥራ አፈፃፀም ምርመራና ኦዲት በማድረግ ለቦርዱ ወይንም ለጠቅላላ ጉባኤው ያሳውቃል፣

18.5. የቦርዱና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው የሥራ ዘመኑ ከመጠናቀቁ ከ 2 ወር በፊት የኦዲት ሪፖርት ያዘጋጃል፣ የርክክብ ሰነድ በማዘጋጀት አዲስ ገቢዎችና ነባሮች እንዲፈራረሙ ያደርጋል፣

18.6. የማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ በሁሉም የስራ ክፍሎች በተግባር ላይ መዋሉን፣ ዕቅዶችና ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው ባጀትና የጊዜ ገደብ መከናወናቸውን ያረጋግጣል፣

<u>አንቀጽ 19፡- የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ</u>

የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በቦርዱ የሚመረጥና የማህበሩን የዕለት ከዕለት ሥራ የሚያከናውን ሲሆን ተጠሪነቱ ለቦርዱ ይሆናል፡

19.1. አባላትን ይመዘግባል የአባላትን ዝርዝር መረጃ ይይዛል።

19.2. የማህበሩን የእለት ከለት የሥራ እንቅስቃሴ ያከናውናል፡

19.3. የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የኢትዮጵያ ማህበረሰብ በሎስ አንጀለስ ሕጋዊ ወኪል ሲሆን፣ ማህበሩን በመወከል የውጭ ግንኙነት ተግባራትን ያከናውናል አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ይደራደራል

19.4. ማህበሩን የሚያጠናክሩ ዕቅዶችን በመንደፍ በቦርዱ ሲፀድቅ በተግባር ያውላል፡

19.5. በየሶስት ወሩ የሥራ እንቅስቃሴ ሪፖርት በጽሁፍ ያዘጋጃል ለቦርዱ ያቀርባል፡.

19.6. የማህበሩ አባላት በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት ተገቢውን አገልግሎት ማግኘታቸውን ያረጋግጣል ግዴታቸውንም እንዲወጡ ክትትል ያደርጋል

19.7. የማህበሩን ዓመታዊ ባጀትና የሥራ ዕቅድ በማዘጋጀት ለቦርዱ ያቀርባል፡ ሲጸድቅም በሥራ ላይ ያውላል፡

19.8. በቦርዱ የፀደቁትን የቋሚና ጊዜያዊ ሠራተኞች ቅጥር ያስፈጽማል ያስተዳድራል፡

19.9. የማህበሩን ዓላማ ለመተግበር የገንዘብና የቁሳቁስ ፍላጎት ለማሟላት የተለያዩ የገንዘብና ቁሳቁስ ማሰባሰቢያ ዘዴዎችን በመንደፍ በቦርዱ ሲፀድቅ በተግባር ያውላል፡

19.10. የማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ በሁሉም የሥራ ክፍሎች በተግባር ላይ መዋሉን፣ ዕቅዶችና ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው ባጀትና የጊዜ ገደብ መከናወናቸውን ያረጋግጣል፣

19.11. የማህበሩን ዓመታዊ ባጀትና የሥራ ዕቅድ በማዘጋጀት ለቦርዱ ያቀርባል፡ ሲጸድቅም በሥራ ላይ ያውላል፡

19.12. በቦርዱ የፀደቁትን የቋሚና ጊዜያዊ ሠራተኞች ቅጥር ያስፈጽማል ያስተዳድራል፡

19.13. እንዳስፈላጊነቱ ጊዜያዊ ኮሚቴዎችን በማቋቋም አጣዳፊ ሥራዎች እንዲከናውኑ ለቦርዱ በማቅረብ ሲጸድቅ ተግባር ላይ ያውላል

19.14. የማህበሩ ገንዘብ ንብረትና መረጃዎች በጥንቃቄ መያዛቸውን ያረጋግጣል፡

19.15. ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ መደበኛ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባ በማድረግ የየኮሚቴዎችን የሥራ እንቅስቃሴ ይገመግማል መመሪያ ይሰጣል፡

19.16. በሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ስብሰባ ላይ የሚገኙት የኮሚቴ አስተባባሪዎች፣ ዋና ጸሐፊውና ዳይሬክተሩ  ሲሆኑ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሌሎች የኮሚቴው አባላት ሊጋበዙ ይችላሉ፡

19.17. ከ $3000.00 በላይ ወጭ የሚጠይቁ ክፍያወችን በቦርዱ እንዲፀድቅ ለቦርዱ ያቀርባል ሲጽድቅ በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡

19.18. የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ስብሰባ የሚጠራውና የሚመራው በዳይሬክተሩ ሲሆን ከኮሚቴ አባላት መካከል 1/2 ኛ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፡

<u>አንቀጽ 20፡- ዳይሬክተር</u>

የኢትዮጵያ ማህበረሰብ በሎስ አንጀለስ በምርጫ ወይም በቅጥር በቦርድ ይመደባል ተጠሪነቱ ለቦርዱ ሲሆን ዝርዝር ሀላፊነቱም፡

20.1. የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴውን የሥራ እንቅስቃሴ በበላይነት ይመራል ያስተዳድራል፡

20.2. የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴውን በሊቀ መንበርነት ይመራል፡ በቦርድ አባላት ስብሰባ ላይ ይሳተፋል ድምፅ ግን መስጠት አይችልም፡

20.ማህበሩን በመወከል የውጭ ግንኙነት ያደርጋል ይደራደራል፡

20.4. የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት በዚህ መተዳደሪያ ደንብ ይተሰጣቸውን የሥራ ሀላፊነት በብቃት መወጣታቸውን ያረጋግጣል ይከታተላል፡

20.5. የሥራ እቅዶችና ፕሮጀክቶች በጊዜው መፈጸማቸውን ይቆጣጠራል፡

20.6. በኮሚቴ አባላት መካከል መልካም የሥራ ምክክርና መግባባት እንዲፈጠር ያበረታታል፡

20.7. የመሕበሩ ገንዘብና ንብረት በአግባቡ መያዙን ያረጋግጣል፡ የተዝረከረከ አሰራርና ብክነት ሲታይ አስቸኳይ የእርምት እርምጃ ይወስዳል፡

20.8. የሥራ ማስኪያጃና ለማህበሩ ተግባር በወጭ ማዘዣ ደብዳቤ ለገንዘብ ያዡ ይልካል በባንክ ቼክ ላይም ይፈርማል፡

20.9. የኮሚቴውን አባላት የዲሲፕሊን እርምጃ አወሳሰድ በሚመለከት የውስጥ መመሪያ ያዘጋጃል።

20.10. በኮሚቴ አባላት አብዛኞቹ (50%) ሲስማሙበትና በቦርዱ ሲጸድቅ በተግባር ላይ ያውላል።

20.11. ዳይሪክተሩን/ሯን ለማገዝ የመዝገብ ያዥ ወይም ሂሳብ ሹም ይቀጠርላታል፣፣

20.12. ሌሎች በቦርዱ የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል።

አንቀጽ 21፡- ዋና ፀሐፊ

ዋና ፀሐፊው በምርጫ ወይም በቅጥር በቦርድ ይመደባል ተጠሪነቱ ለዳይሬክተሩ ይሆናል ዝርዝር ተግባሩና ሀላፊነቱም

21. 1. የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴውን ጽ/ቤት ያስተዳድራል፡

21.2. ገቢ ደብዳቤዎችን ይቀበላል ወጭ ደብዳቤዎችንም ለሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች ያሰራጫል በቅደም ተከተል ፋይል ያደርጋል፡
21.3. የማህበር አባላትን ዝርዝር መረጃ በሚገባ ይይዛል ይጠብቃል
21.4. የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ስብሰባ እንዲጠራ ዳይሬክተሩ ሲፈቅድ ይጠራል፡ የስብሰባውን ቃለ ጉባኤ
21.5. ይይዛል በቅደም ተከተል መረጃውን ፋይል ያደርጋል፡
21.6. የማህበሩ ጽ/ቤት ለአባላት ክፍት እንዲሆን ዕቅድ በማውጣት በኮሚቴው ሲፀድቅ ተግባራዊ ያደርጋል አፈፃፀሙንም ይከታተላል የጽ/ቤት ቁሳቁሶችን ፍላጎት ዝርዝር በመስራት በጀት ይጠይቃል፡
21.7. የየኮሚቴዎችን የሥራ ፕሮጀችት ዕቅዶች በተወሰነላቸው የጊዜ ገደብና በጀት መከናወናቸውን በመከታተል ለዳይሬክተሩ ሪፖርት ያቀርባል፡
21.8. ሌሎች በዳይሬክተሩ የሚሰጡትን ተግባሮች ያከናውናል፡
21.9. ዳይሬክተሩ በማይኖር ጊዜ ዳይሬክተሩን ተክቶ ይሠራል

<u>አንቀጽ 22፡- ልዩ ልዩ ኮሚቴዎችን ስለማቋቋም</u>

የኢትዮጵያ ማሕበረሰብ በሎስ አንጀለስ ቦርድ ወይም የሰራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ማንኛውንም ሥራ በጊዜዓዊነት ወይም በቋሚነት ለማሠራት ነጻ አገልግሎት የሚሰጡ ኮሚቴ ወይም ንኡስ ኮሜቴ ማቋቋም ይችላሉ ኮሚቴው ተጠሪነቱ ላቋቋመው ክፍል ሲሆን የሚከተሉት ተግባርና ሃላፊነት ይኖሩታል፡

22.1. ለማንኛውም ተግባር የሚቋቋም ኮሚቴ ግብረ ሀይል ወይም ንዑስ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ላቋቋመው አካል ይሆናል፡
22.2. የህግና የማህበራዊ ጉዳይ የጤናና የስፖርት የትምህርትና የስልጠና፣ የሴቶችና የህጻናት፣ የወጣቶችና የአዛውንት ጉዳይ ኮሚቴ እንዲሁም አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ችሎታና ፍላጎት ያላቸው ሰዎችን በመጋበዝ እንዲያቋቁሙ ይደረጋል፡
22.3. ቦርድ ማንኛውንም ኮሚቴ ወይም ንዑስ ኮሚቴ ወይም ግብረሀይል አስፈላጊ ሆኖ ካላገኘው ማፍረስ ይችላል፡

<u>አንቀጽ 23፡- የእቅድና ፕሮጀክት ጥናት ኮሚቴ</u>

የዕቅድና ፐርጀክት ጥናት ኮሚቴ በቦርድ የሚቋቋም ሲሆን በስሩ የእቅድና የባጀት የፕሮጀክት ሀሳብ ጥናት ሙያተኞችን በመመልመል የማህበሩን የአጭርና የረጅም ጊዜ ዕቅድና ባጀት ያዘጋጃል የፕሮጀከት ሃሳቦችን ያዘጋጃል ተጠሪነቱም ለዳይሬክተሩ ሲሆን ዝርዝር ተግባርና ሀላፊነቱም

23.1. ከሁሉም ኮሚቴዎች የሚቀርቡ ፍላጎቶችን በማቀናጀት የማሕበሩን ዓመታዊ በጀትና ዕቅድ ያዘጋጃል
23.2. የማሕበሩን ዕድገትና ፍላጎት ግንዛቤ ውስጥ ያስገባ የረጅም ጊዜ የሥራ እቅድ ያዘጋጃል
23.3. የፕሮጀከት ሃሳቦችን ያመነጫል በሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴውና በቦርዱ ሲፈቀድ ዝርዝር ጥናት በማዘጋጀት

23.4. ለለጋሽ ድርጅቶች ( Donors ) መላኩን ይከታተላል
23.5. የተፈቀዱ ፕሮጀክቶችን አፈፃፀም ይከታተላል ለለጋሽ ድርጅቶች የአፈፃፀም ሪፖርት በሰምምነቱ መሰረት በጊዜው መላኩን የከታተላል።
23.6. ማህበሩን ሊደግፉ የሚችሉ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ዝርዝር በማጥናት ሲፈቀድ ፕሮጀክቶች ተዘጋጀተው እንዲላኩ ያደርጋል
23.7. ሌሎች በዳይሬክተሩ የሚሰጡትን ስራዎች ያከናውናል

<u>አንቀጽ 24፡- የሕግና ማሕበረዊ ጉዳይ ኮሚቴ</u>

የሕግና ማሕበራዊ ጉዳይ ኮሚቴ በቦርድ የሚቋቋም ሲሆን በሥሩ የቤተሰብ ችግር ጉዳይ - የኢሚግሬሽን ሕግ ጉዳይ ሙያተኞችን በፈቃደኝነት በመመልመል ለማህበሩ አባላት ሰፊ አገልገሎት የሚሰጥ ክፍል ሲሆን ተጠሪነቱ ለዳይሬክተሩ ነው ዝርዝር ተግባሩና ሀላፊንቱም፡

24.1. በስራ እጦት በጤና ምክንያት በዕድሜ በጾታና በመሳሰሉት ችግሮች ሰለባ የሆኑ የማህበሩ አባላት ተገቢውን ድጋፍና ምክር እንዲያገኙ ያድርጋል፡
24.2. ችግር ቢያጋጥማቸው፣ አባላት ተገቢውን እርዳታና ድጋፍ እንዲያገኙ ከሚመለከታቸው መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር
24.3. አዲስ ለሚመጡ ኢትዮጵያውያን ከአካባቢው ጋር እንዲተዋወቁ የምክር የሞራል የሥራ ማፈላለግ ምክርና ጥቆማ ካስፈለገም ችግር ላለባቸው የገንዘብና የማቴርያል ድጋፍ እንዲያገኙ በማጥናትና ሲፈቀድ በሥራ ላይ ያውላል፡
24.4. ለራሳቸውም ሆነ ለቤተሰቦቻቸው የኢሚግሬሽን ችግር ለሚኖርባቸው ምክርና አገልግሎት ይሰጣል፡ እንደ አስፈላጊነቱ በአካባቢው የሚደረጉ ኢትዮጵያን የሚመለከቱ በዓላትን ያዘጋጃል ዝግጅቱንም በሃላፊነት ይመራል፡
24.5. ሌሎች በዳይሬክተሩ የሚሰጡትን ሥራዎች ያከናውናል፡

<u>አንቀጽ 25፡- የጤናና የስፖርት ኮሚቴ</u>

የጤናና ስፖርት ኮሚቴ በቦርድ የሚመረጥ ሲሆን በስሩ ፈቃደኛ የሆኑ ሐኪሞች ነርሶችና የስፖርት ባለሙያዎችን በማሰባሰብ ለማህበሩ አባላት አገልግሎት የሚሰጥበትን ሁኔታ የሚያመቻች ሲሆን ተጠሪነቱ ለዳይሬክተሩ ነው ዝርዝር ተግባርና ሃላፊነቱም፡

25.1. የማህበሩ አባላት የጤና ችግሮች ትምህርትና መግለጫ በማዘጋጀት በተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን ያሰራጫል ያስተምራል፡
25.2. በአካባቢያችን የሚታዩ የጤና ችግሮችን በማጥናት ተገቢውን የመከላከያና የመቆጣጠሪያ መረጃ ለአባላት ይሰጣል
25.3. በተለያዩ ምክንያቶች ህክምና ለማግኘት ችግር ያለባቸው አባላት በነጻ እርዳታ የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል አቅም ላላቸው የቡድን ኢንአሹራንስ በቅናሽ የሚያገኙበትን ሁኔታ በማጥናት መረጃ ይሰጣል

አንቀጽ 26፦ የትምህርትና ሥልጠና ኮሚቴ

የትምህርትና ስልጠና ኮሚቴ በቦርድ የሚመረጥ ሲሆን ለሥራው ፈቃደኛ የሆኑ የኮምፒውተር ስልጠና የቋንቋ ማሻሻያ (እንግሊዘኛና አማርኛ) ወይምሌላ የኢትዮጵያ ቋንቋ ለወጣቶች የሚሰጥ ሲሆን ተጠሪነቱ ለዳይሬክተሩ ነው ዝርዝር ተግባርና ሃላፊነቱም፣

26.1. አዲስ ለሚመጡ አባላት የእንግሊዘኛ ቋንቋ ማሻሻያ ስልጠና ይሰጣል፣
26.2. የኮምፒውተር ስልጠና ለሚሹ አባሎች ወይም ሌላ የኢትዮጵያ ቋንቋ ስልጠና ይሰጣል፣
26.3. ለወጣቶችና ሕፃናት የአማርኛና ሌላም ቋንቋ የማንበብና የመጻፍ ስልጠና ይሰጣል፡
26.4. የኢትዮጵያን ልዩ ባሕልና ታሪክ ለወጣቶች ትምህርት ይሰጣል፣
26.5. ለሥራው የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን ዝርዝርና በጀት ያዘጋጃል

አንቀጽ 27፦ የሴቶችና ሕፃናት ጉዳይ ኮሚቴ

የሴቶችና ሕጻናት ጉዳይ ኮሚቴ አስተባባሪ በቦርድ የሚመረጥ ሲሆን በስሩ ሁለት ፈቃደኛ ረዳቶችን በመመልመል በሴቶችና ሕጻናት ጉዳይ ላይ ያተኮሩ ሥራዎችን ያከናዉናል ተጠሪነቱም ለዳይሬክተሩ ነው ዝርዝር ተግባርና ሃላፊነቱም፡

27.1. የማህበሩ አባል የሆኑ ሴቶች በፆታቸው ምክንያት የሚደርስባቸውን ችግሮች ካሉ ጥቆማ በመቀበልና በማጥናት ድጋፍና እርዳታ እንዲያገኙ ማድረግ፣
27.2. ሴቶች እንዲደራጁ ማበረታታት፣
27.3. ሴቶች በሚሠሩበት ቦታና በሚኖሩበት አካባቢ የሚደርስባቸውን በደል ማማከር ካስፈለገም የህግ አገልግሎት እንዲያገኙ ያደርጋል፣
27.4. ሴቶች የሃገራቸውን ባህልና ሙያ የሚያንፀባርቁ ተግባራትን በጋራ እያዘጋጁ ለአካባቢው ህዝብ እንዲያሳውቁ ያደርጋል፣
27.5. አቅም የሌላቸውና በሥራ ላይ የተሰማሩ ወላጆች የሕፃናት መዋያ፣ ከትምህርት ቤት መልስ ማቆያ አገልግሎት መስጫ እንዲኖር ዕቅድ ያወጣል ሲፈቀድና በባጀት ሲደገፍ በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡
27.6. ሌሎች በዳይሬክተሩ የሚሰጡትን ሥራወች ያከናውናል

አንቀጽ 28 ፦ የወጣቶች ጉዳይ ኮሚቴ

የወጣቶች ጉዳይ ኮሚቴ በቦርድ የሚቋቋም ሲሆን፣ በሥሩ ሁለት ወጣቶችን በመመልመል በወጣቶች ጉዳይ ላይ ያተኮሩ ሥራወችን ያከናውናል ተጠሪነቱም ለዳይሬክተሩ ነው ዝርዝር ተግባሩና ሃላፊነተም፣

28.1. ወጣቶች የማህበሩ አባል እንዲሆኑ ይቀሰቅሳል ያበረታታል፣
28.2. ወጣቶች ከኢትዮጵያ ባህል ጋር እንዲተዋወቁና ንቁ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ያደርጋል፣

28.3. ወጣቶች ከጎጂ ባህልና ልምድ እንዲርቁ ቅስቀሳና መረጃ ይሰጣል ለወጣቶች መልካም አርአያ የሚሆኑ ጎበዝ ተማሪ ዎችን ፣ስፖርተኞችን ወዘተ በመጋበዝ ጥሩ ሞዴል እንዲሆኑ የወጣቶችን ስብሰባ በማዘጋጀት በመገናኛ
ብዙሃን ያስተዋውቃል፣
28.4. ወጣቶች ባህላቸውን አክባሪ ቤተሰባቸውንና ወገናቸውን አፍቃሪ እንዲሆኑ የማበረታቻና የኪነጥበብ ዝግጅቶችን ያቀነባብራል፣
28.5. ፈቃደኛ የሆኑ ወጣቶች ለህፃናትና በትምህርት ሂደት ችግር ላለባቸው በትርፍ ጊዜአቸው ትምህርት እንዲሰጡ ያደርጋል ያስተባብራል፤

<u>አንቀጽ 29፦ የአዛውንት ጉዳይ አስተባባሪ ኮሚቴ</u>

የአዛውንቶች ጉዳይ አስተባባሪ ኮሚቴ በቦርድ የሚቋቋም ሲሆን ተጠሪነቱ ለዳይሬክተሩ ነው የሚከተሉት ተግባርና ሀላፊነት የኖሩታል የአዛውንት እንክብካቤ ማዕከል እንዲኖር ያደርጋል ለማዕከሉ የሚያስፈልጉትን ቅድመ ዝግጅት ያመቻቻል

29.1. ለአዛውንቶች አስፈላጊውን የአካል ጥንካሬና የሞራል ማበረታቻ ትምሕርታዊ ምክር ይሰጣል
29.2. በሕመም ወይም በተለያዩ ምክንያቶች ችግር ሲያጋጥማቸው ተከታትሎ በመጠየቅ የሞራል ብርታት እንዲያገኙ ጥረት ያደርጋል ያበረታታል

<u>ምዕራፍ አምስት፦ አባልነት (MEMBERSHIP)</u>

<u>አንቀጽ 30፦ የአባልነት መመዘኛ</u>

የማህበሩ አባል ለመሆን የሚከተሉትን መመዘኛዎች ማሟላት ይኖርበታል፡

30.1. ኢትዮጵያዊ ወይንም ኢትዮ-አሜሪካዊ የሆነ/ች ወይንም በጋብቻ የተሳሰሩ
30.2. የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ ተረድቶ የተቀበለና የአባልነት ማመልከቻ የሞላ/ች
30.3. የመመዝገቢያና ዓመታዊ ክፍያ ያጠናቀቀ/ች
30.4. በዕድሜ ከ18 ዓመት በላይ የሆነ/ች

<u>አንቅጽ 31፦ የአባላት መብት</u>

31.1. በመተዳደሪያ ደንብ መሠረት በእኩል የማህበሩ አገልግሎቶች ተጠቃሚ የመሆን፡
31.2. በስብሰባ ላይ ያለምንም ገደብ ሃሳብን የመግለጽ፡
31.አመራሮችን በደንቡ መሠረት ለመምረጥና እንዲሁም ለመመረጥ፡
31.4. በህመም፣ በአደጋ፣ በሥራ ማጣትና ወዘተ ችግር ምክንያት የመመዝገቢያና ዓመታዊ ክፍያ ለመክፈል አቅም ያለመኖር ሲያጋጥም፣ በነጻ የማህበሩ አባል የመሆን፡

አንቀጽ 32፦ የአባላት ግዴታዎች

32.1. በስብሰባ ላይ መገኘት፡
32.2. የመተዳደሪያ ህገ ደንቡን ማክበር፡
32.3. ዓመታዊ የአባል መዋጮውን በደንቡ መሠረት የመፈጽም
32.4. የማህበሩን ንብረቶችና መገልገያዎች በአግባቡ የመጠቀም
32.5. ያለክፍያ የማህበሩ አባል የሆነ/ች ነፃ የኮሚኒቲ አገልግሎት የመስጠት

አንቀጽ 33፦ ከአባልነት የሚያስወግዱ ድርጊቶች

33.1. አንድ አባል በአንቀጽ 30 ላይ የተዘረዘሩትን የአባልነት ግዴታዎች ያለበቂ ምክንያት ለሶስት ተከታታይ ጊዜያቶች ማከናወን ከተሳነው፡ ከአባልነት ይወገዳል
33.2. አንድ አባል ከአባልነት ከመወገዱ በፊት በቅድሚያ የጎደለውን እንዲያሟላ ሁለት ጊዜ ከሥራ አስፈጽሚ ኮሚቴው የጽሁፍ ማሳሰቢያ ከጊዜ ገደብ ጋር ይላክለታል በተሰጠው የጊዜ ገደብ ካላሟላ ከአባልነት መሰርዙን የሚገልጽ ደብዳቤ ይላክለታል፡
33.3. አንድ አባል ከአባልነት ሲሰናበት የከፈለው ክፍያ አይመለስለትም
33.4. ከአባልነት ከተሰረዘ በኋላ እንደገና ለመመዝገብ የሚያመለክት አባል $30.00 መቀጫ በመክፈል ለሁለተኛ ጊዜ እንዲመዘገ እድል ይሰጣዋል፡
33.5 አንድ አባል የግሉን የፖለቲካ የሐይማኖት የብሔር ወዘተ አመለካከት በሌሎች አባሎች ላይ ተጽእኖ ካደረገና በማስረጃ ከተረጋገጠ ከአባልነት ይወገዳል፡
33.6 ማሕበሩ ላልተመዘገበና ከአቅም በላይ ባልሆነ ምክንያት በአባልነት ግዴታውን ለማይወጣ አባል አገልግሎት ለመስጠት ግዴታ አይኖርበትም፡

አንቀጽ 34፦ከቦርድ አባልነት የሚያስወግዱ ድርጊቶች

34.1. ማንናውም የቦርድ አባል ለሶስት (3) ተከታታይ የቦርድ ስብሰባዎች ላይ ሳይገኝ ከቀረ/ች ወይም ከአመቱ የቦርድ ስብሰባዎች ግማሹን ካልተሳተፈ/ች ለመቅረቱም/ቷም አጥጋቢ ምክንያት ከሌለው/ላት በምትኩ/ኳ ሌላ አባል ይተካል፡
34.2. ማንኛውም የቦርድ አባል ማህበሩ የጣለበትን የሥራ ሃላፊነት በአግባቡ ካልተወጣ/ች
34.3. የማህበሩን ደህንነት ለአደጋ የሚያጋልጡ ድርጊቶችን ከፈጸመ/ች በቦርድ ስብሰባ ላይ ከተገኙት ዓባላት በሶስት አራተኛው (3/4) በተደገፈ ድምጽ ከቦርድ አባልነት ሊታገድ ወይም ሊወገድ ይችላል/ትችላለች።
34.4. በቦርድ አባላቱም የተደረገው የማሶገድ ውሳኔ ለተወጋጁ አባል ውሳኔው በተላለፈ በ 10 ቀናት ውስጥ በተመዘገበ የጽሁፍ ደብዳቤ በአድራሻው ይላካል፡
34.5. ለተወጋጁ የቦርድ አባል ስለእገዳው በሚደረገው የቦርድ ስብሰባ ላይ የመገኘ ሃሳቡትናን የማቅረብ መብቱ የተጠበቀ ነው።

አንቅጽ 35፦ ከቦርድ አባልነት ለመልቀቅ የሚሻ/የምትሻ

35.1. የስንብት ደብዳቤ ፕሬዝደንቱ/ቷ ማቅረብ ፕሬዝደንቱ/ቷም ከሆነ/ች ለቦርዱ ዋና ጸሐፊ በማቅረብ ጉድዩ በቀጣዩ የቦርድ ስብሰባ ላይ ይቀርባል፣

35.2. በግልም ሆነ በሌላ ምክንያት ሶስት (3) የሚሆኑ የቦርዱ አባላት ከቦርዱ ቢሰናበቱ እስከ ሚቀጥለው ጠቅላላ

35.3. ጉባኤ ድረስ በጎደሉት በጊዜያዊነት ቦርዱ መተካት ይቻላል፣

35.4. ከሶስት (3) በላይ በድንገት ከለቀቁ ቦርዱ በሰላሳ ( 30) ቀናት ውስጥ አስቸኳይ ጠቅላላ ስብሰባ መጥራት ይኖርበታል።

አንቀጽ 36፦ ተጠያቂነትን በተመለከተ

36.1የማሕበሩ የቦርድና የሥራ አስፈጻሚ ሹማምንቶች፣ ሌሎች የማህበሩ ተቀጣሪ ሠራተኞች እንድሁም ሌሎች በበጎ ፈቃደኝነት ማህበሩን የሚያገለግሉ ሁሉ የማህበሩን ጉዳይ በሚያስፈጽሙበትና በሚያከናውኑበት ጊዜ ለሚደርስ ችግሮች በግል ተጠያቂ ሆኖ ሊያስከስሳቸው አይችልም ይሆን እንጂ በቸልተኝነትም ሆነ በተንኮል ወይም ሐላፊነትን ባለማክበር በማሕበሩ ደንብ መሠረት በተሰጠው/ጣት ሥልጣን ያለ አግባብ በመጠቀም የተፈጸመ መሆኑ ከተረጋገጠ በተፈጸመው ጥፋት ተጠያቂ ይሆናል/ትሆናለች።

36.2ኢማሎአ: ድርጅቱን እንዲያገለግሉ የተመረጡትን የቦርድ ኣባላትንና የድርጅቱን ዳይሬክተር የሚጠብቅ ዋስትና ይገባላቸዋል::(Amended Nov 28, 2020)

አንቀጽ 37፦ የጥቅም ግጭት (መፃረር)

የማሕበሩን ጥቅም ለማስጠበቅና የጥቅም ግጭት ወይም መሰል ሁኔታዋችን በስርአት ለማስተናገድ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ሲከሰቱ የጥቅም ግጭት መፈጠሩን ያመላክታሉ።

37.1 የቦርድ አባል፣ የማሕበሩ ሹም፣ የማሕበሩ ሠራተኛ፣ ወይም በበጎ ፈቃድ የሚያገለግል ሰው (ወይም የነዚህ ሰዎች ቤተዘመዶች) ከማሕበሩ ጋር ላገልግሎትም ይሁን ለቁሳቁስ ግብይት ሲዋዋሉ

37.2 የቦርድ አባል፣ የማሕበሩ ሹም፣ የማሕበሩ ሰራተኞች ወይም በበጎ ፈቃድ የሚያገለግል ሰው (ወይም የነዚህ ሰዎች ቤተ ዘመዶች) የገንዘብ ጥቅም ከሚያገናኞቸው ድርጀቶች ጋር ወይም በቦርድ አባልነት፣ በወኪልነት፣ በሽርክና በመዳደን፣ በባለአደራነት፣ በተጠሪነት፣ በሞግዚትነት ከሚያገለግሉበት ድርጅት ጋር ማሕበሩ ውል ሲፈጽም

37.3 የቦርድ አባል፣ የማሕበሩ ሹም፣ የማሕበሩ ሰራተኞች ወይም በበጎ ፈቃድ የሚያገለግል ሰው (ወይም የነዚህ ሰዎች ቤተ ዘመዶች) የገንዘብ ጥቅም የሚያገናኞቸው ድርጀቶች ከማሕበሩ ጋር ይሚወዳደሩ ወይም የሚጫረቱ ሲሆን

37.4 የቦርድ አባል የማሕበሩ ሹም የማሕበሩ ሠራተኛ ወይም በበጎ ፍቃድ የሚያገለግል ሰው የሥራው ውሳኔዎች ላይ ተጽዕኖ በሚያሳድር መልኩ ስጦታዎችን፣

ግብዣዎችን ውለታ መቀበልን (ከኢማሎአ ሥራ ጋር የማይገናኙ ስጦታና ግብዣን አይመለከትም)
37.5 ሌሎችም የማሕበሩ እንቀስቃሴና በይበልጥም ገንዘብ ነክ ሥራዎችን የሚሰሩ ሰዎች ከጥቅም ግጭት ጋር የሚጓደኑ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ
37.6 የቦርድ አባል፣ የማህበሩ ሹም፣ የማህበሩ ሰራተኛ ወይም በበጎ ፈቃድ የሚያገለግል ሰው ማንኛውንም የጥቅም መጻረርን (የጊዜ መጋጨትንም ጨምሮ Amended Nov 28, 2020) አመላካች የሆኑ ክስተቶች ለቦርድ በማሳወቅ ይማህበሩን ጥቅም ማስጠበቅ ይኖርበታል።
37.7 ቦርዱ ከላይ የተዘረዘሩትን፣ የጥቅም መጻረር አመላካች ያገናዘበ የውስጥ መመሪያ ያዘጋጃል

አንቀጽ 38፡-ሚስጢር ስለመጠበቅ

የቦርድ፣ የማህበሩ ሹም፣ የማህበሩ ሰራተኛ ወይም በበጎ ፈቃድ የሚያገለግል ሰው የጥቅም መጻረርን አስመልክቶ የሚያጋራውን መረጃ በሚስጥር መያዝ አለበት፡ በተጨማሪም የቦርድ አባል፣ የማህበሩ ሹም፣ የማሕበሩ ሰራተኛ ወይም በበጎ ፍቃድ የሚያገለግል ሰው፣ ከማህበሩ ይሚያገኘውን መረጃ ለግሉ ወይም ለቤተሰቡ መጠቀሚያ ሊያደርገው አይገባም።

## ምዕራፍ ስድስት ፡-ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች (MISCELLANEOUS PRROVISIONS)

አንቀጽ 39፡- የምርጫና የድምጽ አሰጣጥ ሥነ ስረዓት

ከማንኛውም ምርጫ በፊት ተገቢውን የአባልነት መስፈርት መሟላታቸውንና በማህበሩ እንቅስቃሴ የሚሳተፉ አባላት ለመምረጥም ሆነ ለመመረጥ ብቃት ያላቸው ምሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡
39.1. አባላት የምርጫ ድምጽ የሚሰጡት በጽሁፍ ለምርጫው በተዘጋጀ ካርድ በሚስጢር ይሆናል
39.2. ቦርዱ ምርጫው በትክክል እንዲካሄድ ለአስመራጭ ኮሚቴው አስፈላጊውን ትብብር ያደርጋል

አንቀጽ 40፡- አስመራጭ ኮሚቴ

የቦርድ ምርጫ አንድ ዓመት ሲቀረው ጠቅላላ ጉባዔው በሚኖረው ዓመታዊ ስብሰባ 5 አባላት ያሉት የአስመራጭ ኮሚቴ ይመርጣል ኮሚቴውም የሚከተሉት ተግባርና ሃላፊነት ይኖሩታል።
40.1. የአስመራጭ ኮሚቴው ፍላጎት ችሎታና ብቃት ያላቸውን አባላት ጥቆማ ከአባላት ይቀበላል
40.2. የአስመራጭ ኮሚቴው የተጠቋሚዎችን የሙያ ብቃትና ያላቸውን ፈቃደኛነት ካጣራ በኋላ ስም ዝርዝርና

40.3. እጩ ተወዳዳሪዎች የትምህርትና የስራ ልምድ ማስርጃቸውን ይሰበስባሉ (Amended Nov 28, 2020)
40.4. የሚወዳደሩበትን የሥራ ዘርፍ ለአባላት ይፋ ያደርጋል ::
40.5. እጩ ተወዳዳሪዎች በመገናኛ ብዙሃን ራሳቸውን እንዲያስተዋውቁ ከተውዳዳሪውቻቸው ጋር ክርክር እንዲያደርጉ ይደረጋል
40.6. ጠቅላላ ጉባኤውን በመጥራት ምርጫው በግልጽ ይካሄዳል፣አብላጫ ድምጽ ያገኙ እጬዎች አሸናፊ
ይሆናሉ ውጤቱም ለጠቅላላ አባላቱ ይገለጻል
40.7. የአስመራጭ ኮሚቴው ትክክለኛ የሆነና አድልኦ የሌለበት ምርጫ መካሄዱን ያረጋግጣል የድምፅ አቆጣጠሩና ውጤቱም ለአባላቱ በትክክለኛ መገለጹን ያረጋግጣል ለተመራጮቹም ለተመረጡበት ዓላማ እንዲዘጋጁ ያደርጋል
40.8. የቦርድ ምርጫ አንድ አመት ሲቀረው ጠቅላላ ጉባኤው በሚኖረው አመታዊ ስብሰባ አስመራጭ ኮሚቴ ይመርጣል።

አንቀጽ 41 ፦ የቦርድ አባላት አመራረጥ

41.1 ባልና ሚስት፣አባት እናትና ልጅ፣ወንድምና እህት በአንድ ላይ የቦርድ አባል ሆነው ማገልገል አይችሉም
41.2 11 (አስራ አንድ) የቦርድ፣ 3 (ሶስት) የኦዲትና የቁጥጥር አገልግሎት እንዲሁም 5 (አምስት) የአማካሪ ሸንጎ አባላት ምርጫ በየ3 (ሶስት) ዓመቱ በጥቅምት ወር (OCTOBER) የመጀመሪያው ቅዳሜ ይከናወናል።

አንቀጽ 42 ፦ የአገልግሎት ዘመን

42.1. የኢትዮጵያ ማህበረሰብ በሎአንጀለስ ማንኛውም በጠቅላላ ጉባኤው የተመረጡ የቦርድና የኦዲት ቁጥጥር የአገልግሎት ዘመን ሁለት (2) ዓመት ነው (Amended Nov 28, 2020)። በድጋሜ ለመወዳደር የሚፈልጉ መሪዎች ወይም ከተጠቆሙ ለ 2ኛ ጊዜ ለመወዳደር ይችላሉማንኛውም የኮሚቴ ዓባል በተከታታይ ከሁለት ጊዜ በላይ ለምርጫ መወዳደር አይችልም።

አንቀጽ 43፦የ መተዳደሪያ ደንቡ የሚሻሻልበት ሁኔታ

43.1. ይህ መተዳደሪያ ደንብ እንደአስፈላጊነቱ ሊሻሻልና ሊለወጥ ይችላል።
43.2. መተዳዳሪያ ደንቡ የሚቀየረው (የሚሻሻለው) ከቦርዱ ዓባላት 2/3ኛው ከጠየቁና፣ ጥያቄው ቢያንስ በስብሰባው ላይ ከተገኙት የጠቅላላ ጉባኤ ዓባላት 2/3ኛው ከተስማሙበት ብቻ ነው።

አንቀጽ 44፦ የማሕበሩ መፍረስ

ማሕበሩን ለማፍረስ ወይም ለመዝጋት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ ብቻ ይሆናል፡

44.1. ከጠቅላላ አባላቱ (3/4) ሶስት አራተኛው በአንድነት ተስማምተው መፍረሱን ሲያጸድቁ ብቻ ነው

44.2. ይህ ከሆነና ማሕበሩ እንዲፈርስ ከተወሰነ ማሕበሩ ያሉበትን እዳዎችና ህጋዊ ግዴታዎች ተጣርተው ያልተከፈሉ እዳዎች ካሉ ለባለ እዳው ተከፍሎ የሚቀረው ገንዘብና ንብረቶች በካሊፎርኒያ ግዛት ውስጥ ላሉ የዚሁ ማሕበር አይነት ተመሳሳይ ዓላማ ለሚያካሂዱ በጎ አድራጊ ድርጀቶች ይከፋፈላል።

አንቀጽ 45፡-የበጀት ዓመት ( ዘመን)
ከ JANUARY 1 (ጃንዋሪ አንድ ቀን) እስከ DECEMBER 31 (ዲሴምበር ሰላሳ አንድ ቀን) ይሆናል።

አንቀጽ 46፡- መተዳደሪያ ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ
ይህ መተዳደሪያ ደንብ (ከመስከረም) SEPTEMBER 28, 2019 ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አንቀጽ 47፡-ትርጓሜ
ትርጉም ይህ ወደ አማርኛ የተተረጎመው መተዳደሪያ ደንብ ከእንግሊዘኛው ሰነድ ጋር የሚያሻማ ወይም የማይጣጣም ትርጉም ሲኖረው የአማርኛው ሰነድ ሃሳብ የፀና ይሆናል።